**በሰሜን አሜሪካ የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ማኅበር**

**AEUP SUPPORT ASSOCIATION – NORTH AMERICA**

1629 K Street, NW, Suite 300. Washington, DC 20006

**Tel: (202) 973-0170 . Fax: (202) 331-3759**

**Web: www.meadusa.org**

**ለመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ፓርቲ) ሥራ አመራር አባላት** **ሚያዚያ 8፣ 2003**

**አዲስ አበባ**

**<u>ጉዳዩ፤ በመኢአድ ሥራ አመራሮች መሀከል ስለተፈጠረው ችግር የሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ማህበር ልዩ መግለጫ</u>**

በመሠረቱ በስሜን አሜሪካ የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ማህበር ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ ፓርቲውን በገንዘብ፤ በዲፕሎማሲና የፓርቲውን ፕሮግራምና የሥራ እንቅስቃሴዎችን በተቻለ አቅም ሲደግፍ ሲያስተባብርና ሲያስተዋውቅ እነሆ ከሰባት ዓመት በላይ አሳልፎአል። በነዚህ ጊዚያቶች የድጋፍ ማህበራችን ያለውን አቅም ሙሉ በሙሉ ተጠቅሞ አገልግሎቱን ለመስጠት የሚፈለገውን ድጋፍና እርዳታ ለፓርቲው እንዳያደርግ በተለይም ከሀገር ቤት በፓርቲው አመራር በሚነሱ ችግሮች ሳቢያ በየጊዜው እየተዳከምን እንድንሄድ ሆኖአል። ሆኖም ማህበራችን አሁንም የሚደርሱበትን ችግሮች እየተቋቋመ አንድነታችንን ጠብቀን እስከዛሬ ደርሰናል። ለወደፊትም ድርጅቱ በአቋሙ ጸንቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከግፍ አገዛዝ ሥር እስከሚላቀቅ ድረስ ትግሉን ከቀጠለ ከጀርባው በደጀንነት እንደምንቆም ለማሳወቅ እንወዳለን።

ድርጅታችን መኢአድን የሚደግፈው ፤አስተማማኝ የህዝብ መሠረት ያለው ብሔራዊ ፓርቲ መሆኑን በማመን ነው። መኢአድ ክጥንት መሠረቱ ጀምሮ በየጊዜው የደም መስዋዕትነት እየተከፈለበት አሁን ላለበት ደረጃ ሊደርስ የቻለው ጠላቶቹን፣ በተለይም በሥልጣን ላይ ያለውን የወያኔ ፓርቲና መንግሥት፣ እንዲሁም ወዳጅ መስለው የቀረቡ አፍራሾችን በመቋቋም እንደሆነም ይታወቃል። በዚህ ሂደትም ከእርሻ ማሳቸው የተፈናቀሉ ገበሬዎችን፣ ከሥራቸው የተባረሩ ሠራተኞችን፣ ለስደት የተዳረጉ ኢትዮጵያውያንን፣ በየእሥር ቤቱ የሚማቅቁትን፣ መተኪያ የሌለውን ውድ ህይወታቸውን የሰጡትን ሁሉ፣ በተለይም በምርጫ 97 በጅምላ የተጨፈጨፉትን ስናስብ፣ በቀጥታ የዚህ መስዋዕትነት ተካፋይ አለመሆናችን እየተስማን ልባችን በህዘን ይደማል።

ይህ መስዋዕትነት የተከፈለው ከደጋፊዎች አንስቶ በየደረጃው ባሉ አባላትና መሪዎች በመሆኑ የፓርቲውን ጥንካሬ ያመለክታል። ፓርቲው የመላው ኢትዮጵያውያን በመሆኑ በኢትዮጵያ ግዛቶች፣ የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ ጽ/ቤቶችን በመክፈት መዋቅሩን ዘርግቶ ለመንቀሳቀስና ለማደራጀት የቻለ ፓርቲ መሆኑን እናውቃለን። መኢአድ እንኳን እራሱን የሚያስተዳድር ሕግ ቀርቶ መላው የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃ አውጥቶ ሊያስተዳድር የሚችል በሊበራል ዲሞክራሲ እምነት ላይ የተመሠረተ ግልፅ የፓርቲ ፕሮግራም ነድፎ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው።

ከፍ ብሎ የተጠቀሱት የፓርቲው ጠንካራ ጎኖች እያሉ በቅርቡ ከፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ፍጻሜ ማግሥት ጀምሮ በፓርቲው የሥራ አስፈጻሚ አባላት መሀከል የተፈጠረው አለመግባባት ድርጅቱን ከፍተኛ አደጋ ላይ ከመጣሉም በላይ በፓርቲው አመራር ላይ ጥያቄዎች ማስነሳቱ አልቀረም። ይኸውም የተፈጠረው ችግር በጠረጼዛ ዙሪያ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መፍትሄ ማግኘት ሲገባው ወያኔ ፍርድ ቤትና ምርጫ ቦርድ በመወሰዱ ችግሩን አባብሶ ፓርቲውን በቆራጥነት ለብዙ ዓመታት ሲመሩ የነበሩ አባላት እስከ ሁለት ዓመት ከአራት ወሮች በሚደርስ የእስር ዘመን ወደ ወህኒ እንዲወርዱ ተደርጎአል። ይኅም ከመድረሱ በፊት ችግሩ መፍትሄ ያገኛል ብለን ለወራቶች ከጠበቅን በህዋላ ማህበራችን ለፓርቲው ያለውን ተቆርቋሪነት መሠረት በማድረግ ችግሩ እንዲፈታ የሚከተለውን ጥረት አድርገናል፤

- ማህበራችን በአንድ በኩል አቶ ያዕቆብ ልኬን በሌላ በኩል ደግሞ አቶ ማሙሸት አማረን ለየብቻ በማነጋገር ጉዳያቸው በሽምግልና እንዲፈታ በመጀመሪያ ስምምነት ላይ ከተደረሰ በሕዋላ ፍጻሜ ላይ ሲደርስ አቶ ያዕቆብ ልኬ ጉዳዩ በፓርቲው ሕገ ደንብ፤ የዲስፕሊን ደንብና በፍርድ ቤት የሚፈታ እንጂ በሽምግልና እንዳልሆነ በመግለጻቸው ሳይሳካ ቀርቶአል።

- በማህበራችን መላው አባላት ጥያቄ መሠረት ሁለቱም ወገኖች ያልተስማሙበትን ምክንያት እና ለችግሩም መፍትሄ በምክክር ለማስገኘት የቴሌ ኮንፈረንስ እንዲዘጋጅ በተወሰነው መሠረት፣ የፓርቲውን ፕሬዘደንት ኢንጅነር ኃይሉ ሻውልንና ምክትሉን አቶ ያዕቆብ ልኬን በአንድ በኩል፣ በሌላ በኩል ደግሞ እነ አቶ ማሙሸት አማረን አቅርበን በጠቅላላው ከ6 ሰዓት ላላነሰ ጊዜ ለማነጋገር ብንሞክርም ውጤት ሊያመጣ አልቻለም። ለዚህም ምክንያቱ በፕሬዘዳንቱና በምክትላቸው በኩል ችግሩ የሚፈታው በፓርቲው ውስጠ ደንብ በዲስፕሊን ኮሚቴ ብቻ ነው ሲሉ እነ አቶ ማሙሸት አማረ ግን በጠረጴዛ ዙሪያ በመነጋገር ነው በማለት በተቃራኒው በመቆማቸው ነው።

- ማህበራችን ከከፍተኛው የሥራ አስፈጻሚ አባላት ጋር ያደረገው ውይይት እና መፍትሄ የማፈላለጉን ሂደት አለመሳካት ሲረዳ ከፓርቲው የዞን ኀላፊዎች ጋር በጉዳዩ ለመምከር በመወስን በየደረጃው የሚገኙ የዞን ኀላፊዎችን በየተራ በቴሌኮንፈረንስ እየጋበዘ አነጋግሮአል። ለዚህም የዞን ኀላፊዎቹ የስጡት የመፍትሄ ሀሳብ የተፈጠረው ችግር በሥራ አስፈጻሚው የማይፈታ ሆኖ በመገኘቱ ፤ቅሬታቸውን ለፓርቲው ፕሬዘዳንት በደብዳቤ ማሳወቃቸውን ገልጸውልናል። በፓርቲው ሕገ ደንብ መሠረትም የሚከተለው የሥልጣን አካል 105 አባላት ያሉት የላዕላይ ምክር ቤት በመሆኑ ማንኛውም ጉዳይ በዚያ እንዲታይ እንደሚፈልጉና ደንቡም እንደሚፈቅድና እንደሚደግፋቸው በተደጋጋሚ ገልፀውልናል።

- ማህበራችን ይኀንኑ የዞን ኀላፊዎችን ሀሳብ በመያዝ ችግሩን በፓርቲው ውስጠ ደንብ መሠረት እንዲፈታ አስፈላጊ መረጃዎችን ይዘን ለአቶ ያዕቆብ ልኬ ተማጽኖ ብናቀርብም አሁንም ከሕግና ከዲሲፕሊን ኮሚቴ እርምጃ ውጭ መፍትሄ እንደሌለው አስታውቀውናል።

- ማህበራችን አሁንም ለጉዳዩ መፍትሄ ለመሻትና የቃላት ጦርነቱንም ሆነ በድርጅቱ ላይ በሁሉም ወገን ተባብሶ ጉዳት እያደረሰ ያለውን የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ለማስቆምም ጭምር ያኣዲስ አበባ ክፍለ ከተማዎች ሰብሳቢዎችን፣ የወጣቶችና የሴቶች ጉዳይ ኀላፊዎችን፣ የሙታን ቤተስብ ተወካዮችና ለፓርቲው ቅርበት ያላቸውን ግለስቦች ጭምር በማነጋገር የተረዳነው ፤ችግሩ ሊፈታ የሚችለው በፓርቲው ውስጠ ደንብ መሠረት በውይይት ብቻ እንደሆነ ነው።

ሁኔታው ከፍ ብሎ እንደተዘረዘረው፣ ችግሩ በፓርቲው መዋቅር ሕግና ደንብ መሠረት እንዲፈታ ያለዕረፍት ጥረት በማድረግ ላይ እያለን ነው የፓርቲው ምክትል ተ/ፕሬዘዳንት የነበሩት ዶ/ር ታዲዎስ ቦጋለ እና አቶ ግርማ ነጋ በሁለት ዓመት ከአራት ወር እና በአንድ ዓመት ከ8 ወራት እሥር ወደ ወህኒ ቤት መውረዳቸውን የሰማነው። በዚህ ሳቢያም ማህበራችን ከ15 በላይ ከሚሆኑ የአሜሪካ ክፍለ ከተሞች ከተሰባሰቡ አባላቱና ደጋፊዎቹ ጋር ሚያዝያ 8 ቀን (አፕሪል 16) አሰቸኳይ ጠቅላላ ስብሰባ አድርጎ የፓርቲውንና የማህበራችንን ህልውና ከጥፋት ለማዳን የሚከተሉትን የአቅዋም መግለጫ ለማውጣት ተስማምቷል።

- ለአንድ ፓርቲ እድገትም ሆነ ውድቀት የመጀመሪያዎቹ ተመስጋኝም ሆነ ተወቃሽ የፓርቲው ወይም የማናቸውም ድርጅት ዋና መሪ መሆኑ አያጠያይቅም። በዚህ ረገድ የፓርቲው ፕሬዘደንት ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ፓርቲውን ለማሳደግ የቻሉትን ያህል የደረሰበትን ችግር ባለው ውስጠ ደንብ መሠረት እንዲፈታ ማድረግ እየቻሉ፣ ከዚህ በፊት እራሳቸውንና የትግል ጓደኞቻቸውን ያለምንም ጥፋታቸው ፍትህ በሌለበት ፍርድ ቤት የእድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ለፈረደባቸው የወያኔ ፍርድ ቤት የትግል ጓደኞቻቸውን  አሳልፈው በመስጠታቸው እጅግ  አዝነናል። ለዚህም የተባበሩ ወገኖች ሁሉ በታሪክ ከመጠየቅ እንደማይድኑ ሊገነዘቡት ይገባል።

- የወያኔ ፍርድ ቤት/መንግሥት ተብዬዎችም በፓርቲ አሠራር ውስጥ በመግባት አጋጣሚውን በመጠቀም በእነ ዶ/ር ታዲዎስ ቦጋለ ላይ የወሰደውን የተዛባና የፖለቲካ ፍርድ አጥብቀን እንቃወማለን።

- አሁንም በሌሎች የፓርቲው አባላት ላይ የፍርድ ውሳኔ ቅጣት ለማስወሰን የሚደረገው ጥረት በአስቸኳይ እንዲቆም ማህበራችን በጽናት ይጠይቃል።

- ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው የፓርቲው ችግር ሊፈታ የሚችለው በፓርቲው ህግ፣ ደንብና ሥርዓት በመሆኑ፣ በአሁኑ ወቅት ችግሩ እየተባባሰ እንጂ መፍትሄ እያገኘ ባለመሆኑ ወደሚቀጥለው የሥልጣን ተዋረድ ተላልፎ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እልባት እንዲያገኝ እንጠይቃለን። በዞን ኀላፊዎቹና በአብዛኛው አባላትና አመራር ጥያቄ መሠረት የላዕላይ ምክር ቤቱ በአስቸኳይ ተጠርቶ ችግሮቹን ሁሉ መርምሮ እንዲፈታ እናሳስባለን።

- ፓርቲው የራሱን ችግር በራሱ ለመፍታት በሚያደርገው እንቅስቃሴ የሚያስፈልገውን የገንዘብ ወጪ ማኅበራችን እንደሚሸፍን በሙሉ ድምፅ ተስማምተናል።

- በአሁኑ ወቅት ማናቸውም የአባላት መዋጮም ሆነ የሕዝብ ድጋፍ በችግሩ ምክንያት የመጨረሻው ወለል ላይ በመሆኑ ከፍ ብሎ የዘረዘርናቸውን እጅግ ጠቃሚ አስተያየቶች በአስቸክዋይ በሥራ ላይ በማዋል የደጋፊዎቻችንን እምነት እንደገና ተላብሰን የድጋፍ ሥራችንን እንድንቀጥል፣ ፓርቲውም በውስጡ የተፈጠረውን ውዝግብ አቁሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ ወቅት እየደረሰበት ያለውን የመከራ ጩኸት ሰምቶ፣ ትግሉን እንዲመራ አስፈላጊውን ሁሉ እንድታደርጉ መሪዎቹን አደራ ጭምር እንጠይቃለን።

- በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በተፈጠረው ችግር ለእሥር የተዳረጉ የፓርቲው አባላትና ቤተሰቦቻቸውን መኢአድ የመርዳትና የመንከባከብ ኀላፊነት አለበት ብለን እናምናለን። ማኅበራችንም ይኅንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ተስማምቶአል።

- የግል የሥልጣን ፍላጎትን ከማንጸባረቅ ይልቅ፤ ለፓርቲው ዓላማና ህልውና ቅድሚያ መስጠትና ችግሮችን በጋራ፤ በስምምነትና በመቻቻል መፍታት፤ ለፓርቲው ጠቅላላ አባላትም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንካራና አስተማማኝ መልእክት እንደሚያስተላልፍ አንጠራጠርም።

በመጨረሻም እኛ በሰሜን አሜሪካ የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ማህበር አባላት በሙሉ፣ ለወደፊቱም እንደበፊቱ የመኢአድ ዓላማን በጽናት ከሚያራምዱ አመራሮችና አባሎቹ፣ ከራሳቸው ይልቅ የድርጅቱን፣ የሀገሪቱንና የሕዝባችንን ጥቅም ከሚያስቀድሙ ጋር እስከ ነፃነት ድረስ ተሰልፈን ለመርዳት ቃላችንን እናድሳለን። በዚያው አኳያ የኢትዮጵያ ሕዝብ አለኝታ የሆነውን ፓርቲያችንን ለመከፋፈል፣ ለማዳከምም ሆነ ከትግሉ አትኩሮት እንድንዘናጋ የሚደረግን ማንኛውም ዓይነት ተንኮልና ሙከራ በፅናት ተግተን የምንጠብቀው ሲሆን ተንኮሉ ሲከሰትም አጥብቀን እንደምንታገለው እናሳስባለን።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ

በሰሜን አሜሪካ የመኢአድ ድጋፍ ማህበር